# ሳያጣሩ ወሬ ሳይገድሉ ጎፈሬ

## ዋለልኝንና ያን ትውልድ ለቀቅ

ሀማ ቱማ

ስለ ሀገራቸውና ለሀገር ውድ ሕይወታቸውን ስለሰጡት ቅንጣትም ሳያውቁ ወይም ጥራዝ ነጠቅ ግንዛቤን ይዘው የክስና ስድብ ውርጅብኝ የሚያሰሙትን አንቱ በሉኝ ባዮች ጉራቸውን ልዋስና ግጥም የቻልኩ መስሎኝ የነበረ ሰሞን ፅፌ የነበረውን የራሴን አንዷት ግጥም ልጥቀስ --

“ መሬት ያራሰውን ያንን የደም ጀግና
መሬት ያቀላውን የእሷን ደም የጀግና
ጠቅጥቆ ያለፈ ምራቁን የተፋ
ታሪክን አዋራጅ ሀገር የሚያጠፋ፡፡ ”

የለየላቸው አድሀሪዎች እየመሩና የቀይ ሽብር አራማጆች አጀብ ሆነው ዘመነ ትምክህትን ናፋቂዎች ሁሉ ድንገት ትዕዛዝና የክተት አዋጅ የመጠባቸው ይመስል ለለውጥ በታገለው ትውልድ ላይ ከፍተኛ የስም ማጥፋት ዘመቻን ከፍተዋል፡፡ በዚህም መሰረት ህይወቱን ለሀገር ና ለዓላማው ሰጥቶ ያለፈውን ዋለልኝ መኮንንን በተለይ መዝለፍ አብዝተዋል፡፡ በዋለልኝ ሽፋን ያ የጊዜው የተማሪዎችና የተራማጆች እንቅስቃሴ በአድሀሪያን እየተወነጀለና እየተጠ ቃ ነው፡፡ ታዲያ ታሪክ ጠባቂ ካጣ ሊቆሸሽና ሊበረዝ ሊሰረዝ ስለሚችል ሁሉም ዘብ መውጣት አለበትና የድርሻዬን ልወጣ እነሆ ተነስቻለሁ፡፡

“ ይድረስ ብለው ፃፉ
ምስጢር ብለው ጣፉ
ተራራ አንቀጠቀጥን ሲሉም ለፈለፉ
ሀቅን ገድለው ቀብረው ቅጥፈት ባነገሱ
ያ ትወልድ እያሉ ትወልድ ባወገዙ ”

ነው ቁም ነገሩ፡፡ በአፄው ዘመን የተካሄደውን ታሪካዊ ትግል በማንቋሸሽ የሚያቀርቡ በሚከ ተለው መልክ ሊገለፁ ይችላሉ፤

- የአፄው ዘመን  የስልጣን ተካፋዮችና የጭቆናው አራማጆች
- የደርግ ዘመን ወንጀለኞች
- ትግሉ ሲካሄድ በቦታው ያልነበሩ ወይም አድሀሪ ሚና የነበራቸው

- ዛሬም በዚሁ አያይዘው ኢሕአፓን ሊያጠቁ የተነሱ ክፍሎች
- ተራማጅ የነበሩና ዛሬ አድሀሪ ሆነው የቀድሞ ታሪካቸው ላይ ተፍተው የሚዋረዱ።

ከዚህ ጥርቅም ውጪ ያው በባዕዳንም ተገዝተው የሚጮኹት አሉ። ተገንጣዮችና አስገንጣዮ ችም የራሳቸው ተልዕኮ አላቸው። የዋለልኝን ስም ወያኔ ሊጠቀም መሞከሩ አንድ ምልክት ነው። በቅድሚያ መታወቅ ያለበት ማንም ሰው ያን ትውልድ ሆነ፣እንቅስቃሴውን ሆነ ግለሰቦ ችን በፅሞና የመተቸት መብቱ የተጠበቀ ነው። በዚህ በዚያ ስህተት ነበር፣ ደጉ ወይም ፀጋው ይኸ ነበር ብሎ በሚዛንና በገንቢ መልክ መገምገሙ በእርግጥም አስፈላጊ ነው። ይህን የሚቃ ወም አይኖርም። ግን በፈጠራ ታሪክ የሀሰት ወሬን እያራገቡ ትውልዱንም  እንቅስቃሴውን ም ለማንቋሸሽና ታሪክን ለማጥፋት የተከፈተው ዘመቻ መወገዝ ያለበት ነው። አንድ እናቱን  ሳይቀር ሲአይኤ ብሎ ሊከስ የሚዳዳውና ምሁር ነኝ በማለቱ ብቻ ምሁር ለሚለው ቃል ባለጌ ትርጉምን የሚሰጥ ግለሰብ ለምሳሌ ዋለልኝን የሲአይኤ ቅጥረኛ ከማለቱ ሌላ የታገሉት ን ሁሉ የሻዕቢያ ቅጥረኞች ብሎ ሊያዋርድ ሞክሯል። ሌሎችም የራሳቸውን መጥፎ ሚና አሊያም የዛሬን የራሳቸውን አቋም ለማራገብ ብቻ ያን ትውልድ በደፈናው  እየቀጠቀጡ ናቸው። ታድያ መከላከል ይነሰን?

በግለሰብ ደረጃ የያኔው እንቅስቃሴ አካል የነበርኩ ሲሆን ዋለልኝን ባውቀውም በጣም በቅርቡ አልነበረም። ሆኖም የተማሪው እንቅስቃሴ አባል ነበርኩና በአድማ ኮሚቴዎች ስራ ዙሪያ ተገናኝተናል። ሀገር ወዳድና ቆራጥ ጓድ ነበር ማለት እችላለሁ፣ በመስዋዕትነቱም ያስመሰከረውይህንኑ ነው። ዋለልኝና ሌሎቹ ጀግና ወጣቶች አይሮፕላን ለመጥለፍ ሲሞክሩ ተገድለዋል። ስለዚህ ጠለፋ ዝርዝሩን የሚያውቁት አልተናገሩም፣ የሚለፍፉት ደግሞ የሚያ ውቁት የለም፡የእነ ዋለልኝ እርምጃ ግን የሻዕቢያን ተልዕኮ ለማሟላት አልነበረም። ዋለልኝ ለኢሕአፓ ምስረታ  በሀገር ሆኖ ከእነ ፀጋዬ ደብተራው ጋር አብሮ ሆኖ የበኩሉን ታግሏል።  በዚህ ደረጃም አብረን ታግለናል ማለት እችላለሁ። ስለ ከሸፍ ጠለፋው ሙከራ የሚያውቁ ት ያውቃሉ--ያ ታሪክ እስኪፃፍ ግን በበኩሌ በዚሁ ትቶ ማለፉን እመርጣለሁ። እኔ የማተኩረው ዋለልኝና ያ ትውልድ ለሀገሪቷ የብሄረሰብ ችግር፣ለኤርትራ ጦርነትና አንጻ አወቅኩ ባይ በቅርቡ እንዳለው ደግሞ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ለመሆኗም(!) ተጠያቂ ናቸው የሚለው ላይ ነው።

ኮሶን ላለቀመው ይመር አይመስለው ነውና ያኔ ላልኖሩት ወይም ቢኖሩም መከራውን ቀማሽ ያልነበሩት ስለ አፄው ስርዓት ግንዛቤያቸው ቢንሸዋረር የሚገርም አይሆንም። ኃይሌ ኃይሌ የሚሉት ታሪክን አያውቁም፣አልተማሩም ወይም ረስተዋል። ዓይኑን ለከፈተና ለማወቅ ለጣረ ግን ግፉ ሞልቶ ተርፎ ነበር። በሁሉም መስክ። እነ ዋለልኝ ዓይነቶቹ በክፍለ ሀገራት

ከድህ ቤተሰብ የተወለዱ ተማሪዎች ስለ ነበረው ችግርና ስለ ፊውዳል ስርዓቱ አስከፊነት መፅሀፍም ማንበብም መጠየቅም አልነበረባቸው:: ዋለልኝ የኢትዮጵያን ሕዝብ ያውቅ ነበር-- እውቀት ደግሞ አንፃራዊ ነውና ዛሬ የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች የተባሉት ለምሳሌ ስለ ጭቁኑ ህዝብ ሰቆቃ ያላቸው ግንዛቤ ደካማ የሆነ ህብታሞች መሆናቸውም በማነፃፃር ሊታይ የሚገባው ነው:: ለማንኛውም ዋለልኝ ላይ ከ 39 ዓመት በኋላ የተከፈተው መጥፎ ዘመቻ በተለይ በእሱ ተፅፎ በዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ማህበር ጋዜጣ ላይ የወጣውን ፅሁፍ ይመለከታል:: የዋለልኝ ፅሁፍ ያወጣው ያበጠው ይፈንዳ በሚል ርዕስ እንደነበር ትዝ ይለኛል:: ርዕሱ ፍላጎቱን ገላጭ ሆኖ መወሰድ ሲገባው ሀቁን በተናገረ ተወገረ ሆነና ዛሬ በመጥፎ ይወገዘበታል:: ያበጠው ይፈንዳ ያለው በዚያን ጊዜ የብሄረሰብ ጭቆና መኖሩ የሚ ደረግ እንጂ የሚወራ ስላልነበረ ነው:: በመሆኑም የማስደንገጥና የማንቃት/የኡኡ ጩኸት ቃና/ ይዞ የወጣው ፅሁፍ መልዕክቱ ኅበዝ ይህ ችግር አለ እኮ፤ ሀገርን ሊጎዳ ሊያጠፋ ይችላል እኮ፤ እንየው፤እንወቀው እንነጋገርበት ለማለት ነበር:: የዋለልኝን ፅሁፍ (1) ሁኔታውን በማ ጋለጡ (2) በሰጠው መፍትሄ (የራስን ዕድል በራስ የመወሰን ሙሉ መብት) የሚተቹት አሉ::

ወደ ይዘቱ ከመግባታችን በፊት ግን ያ መሬት ለአራሹ፤ዴሞክራሲ ለጭቅኑ ሕዝብ ብሎ የታ ገለው የእነ ዋለልኝ ትውልድ በዚያን ጊዜ ያጋጠሙት የስርዓቱ ዕድሮች ምን ምን እንደነበሩ ማወቅ ያስፈልጋል:: ዋለልኝ ኢትዮጵያ የብሄረሰቦች እስር ቤት ሆናለች ብሎ ፅፏል ( ፕሪዝ ን ኦፍ ናሽናሊቲስ የሚለውን ተርጉሞ ነው):: ይህ አልዋጥ ያላቸው ኢትዮጵያን ነቀፈ ብለዋ ል:: ኢትዮጵያ የሕዝቧ ሁሉ እስር ቤት ነበረች:: ይህ ነበር ሃቁ:: በአፄው ኢትዮጵያ የብሄረሰቦች ጭቆናና የህይማኖትም ልዩነት/አድልዎ ነበር:: በተማሪው እንቅስቃሴ ተባብረው ና ኢትዮጵያ ብለው የታገሉት ሁሉ (ኤርትራ የተወለዱትም ጭምር) ይህንን የጭቆና ሁኔታ በዴሞክራሲ መፍትሄ እናስወግድ ብለው በቀና የተነሱ ነበሩ:: ተቺዎቹ ረስተው ወይም ሸፋፍነው የሚያልፉት አቢይ ሀቅ ግን ተማሪዎቹ/ተራማጆቹ መሬት ለአራሹ፤ድህው ይማር፤ ድህነት ወንጀል አይደለም፤ ዴሞክራሲያዊ መንግስት ይቋቋም ብለው መታገላቸውን ነው:: ሀገር ሊከፋፍሉ ተነሱ የሚለው ዛሬ በዋለልኝ ላይ ተነጣጥሮ የሚለፈፈው ክስ በዋና መልኩ ኢሕአፓን መወንጀያ መሆኑንም እናውቃለን:: ለጠቢብ አንድ ቃል ይበቃል የሚለው ስለተረሳና አወቅን ሰለጠን ባዮቹ ደግሞ ላልተገራ ጊዜ ያልተገሩ ሊቆች ሆነዋልና በዚህ ጥያቄ ላይ ደግሞ ተደጋግሞ ሀቁ ቢነገርም መስማት ያለበት ጆሮአቸው ላይ ተኝተው እያንኮራፉ ነው:: ሳንታክት ግን መድገም አለብንና እነሆ በሀ ለ ሐ መልክ--

ሀ / ተማሪዎች፤ ዋለልኝ፤ ኢሕአፓ፤ተራማጆች የብሄረሰብና የኤርትራን ችግር አልፈጠሩም፡ ለ / የኤርትራ ሽምቅ ተዋጊ ግንባር /ኢኤልኤፍ ጀብሀ/ የተቋቋመው በአውሮጳ አቆጣጠር በ1960 ነው::

ሐ / የመጀመሪያው የመሬት ለአራሹ ሰልፍ በዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የተካሄደው በአውሮጳው ያን አቆጣጠር በ1965 ዓ.ም. ነው።
መ / የሜጫ ቱለማ እንቅስቃሴ ሲካሄድ ዋለልኝ የተባለውን ፅሁፍ ገና አልፃፈም ነበር። በኦጋዴን፣ በባሌ ፣ደራሳ ይባል በነበረው ወዘተ የአርሶ አደሮች አመፆች ሲካሄዱና በዚህም በዚያም የመሬትና የብሄረሰብ ጭቆና ጉዳይ ተያይዞ ሲነሳ የኢትዮጵያ ተማሪዎችና ተራማጆ ች ገና የብሄረሰብ ጥያቄ የተባለውን አላነሱም ነበር።

ይህ እንግዲህ ቢፈጩት፣ ደቀቀ፣ ተነነ የምንለው ሀቅ አይደለምና ክስ ደርዳሪዎቹ ዋለልኝን ለቀቅ፣ ያን ትውልድ ለቀቅ አድርገው ወደ ስርዓቱ ወደ አፄው አገዛዝ ዓይናቸውን መመለስ ከቻሉ መመለስ አለባቸው። የነበረው አገዛዝ ያበላሸውን ለማስተካከል፣ዋለልኝና ጓደኞቹ ከዚያም ኢሕአፓ በቻሉበትና ባመኑበት መንገድ ሞከሩ። ያ ትውልድ ወደ ግራ ለምን አዘነበ ለ፣ ለምን ርዕዮቱም በዚያ መንገድ ሆነ ለሚለው እንዲሁ ተደጋግሞ ገለፃ ተሰጥቷል። ለሀገሪ ቷ ችግር ዛሬ ኢትዮጵያ ወይ ሞት የሚሉት ያኔ ያቀረቡት መፍትሄ አልነበረም። በዘመነ ደርግም በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ምላሽ ለመስጠት የተደረገው ሙከራ የግራ ኃይሎች ተፅዕ ኖ ውጤት ነው። በየካቲት አብዮት ጊዜም ኢትዮጵያውያን እስላም ክርስቲያን ሳይሉ የሀይ ማኖተ ተቃውሞን አውግዘው ትልቅ ሰልፍ አደረጉ እንጂ ዛሬ አንደሚሞከረው ልዩነትና አድልዎ የለም ብለው እንደ ሰጎን አንገታቸውን ከአሸዋ አልደበቁም። በአጭሩ አብዮት የሚ ያሻው የተበላሸ ኋላ ቀር ስርዓት ነበርና ያ ትውልድ ያን ስርዓት ለማውደም ያደረገውን አስተዋፅዖ ይኮራበታል። ሰማዕት የሆኑት እነ ዋለልኝም ጀግና ቢባሉ ሲያንሳቸው ነው። እነሱን የሚያጠቁትና የሚዘልፉትም ሲመዘኑ ገለባ፣ ሲመረመሩ የተቀማጭ ምላሱ ምላጭ ሆነው የሚቀሩት። ያበጠው ይፈንዳ ቢባል ያበጠ ና ያመረቀዘ ስርዓተ ነበርና ሲያንስ ነው። በዝርዝር ወደ አስከፊው ጭቆና የማንገባው ለዘረኛው ወያኔ ወፍጮ ባቄላ ላለመቀበል ብለን ብቻ ነው።

ወደ መፍትሄው ስንመጣም የራሰን ዕድል በራስ የመወሰን መብትን በቀረበበት ሁኔታና መንፈስ መቀበል/መረዳት ያቃታቸው ሁሉ ቢነገሩ ቢነገሩ አንሰማም ብለው የሚወዱት አገዛዝ ሀገርን ለግንጠላ አመቻችቶ እያለ (የአፄውም የደርጉም) ዴሞክራሲያዊ ምላሽ ሰጥተው መፍትሄ የፈለጉትን አምርረው ያወግዛሉ። ዛሬ የወያኔን ፈለግ ተከትለው ዘር ቆጠራ የገቡ ጥቂቶች አይደሉም። ሀገራችን ኢትዮጵያ ብሄረሰባችን ኢሕአፓ ሳልነውም በየጊዜው የለም ብሄረሰባችሁ ይህ ያ ነው እየተባልን አለ ። ጉድ!! በተማሪው እንቅስቃሴ የተሳተፉትን በአብዛኛው ከሰሜን በማድረግ ሌላው እንዳልታገለና እንደተነዳ አድርገው ማቅ ረብ የሚፈልጉ አሉ። ሌሎች ደግሞ ወያኔ ለስልጣን ስለበቃና ሻዕቢያም ያሰበው ስለሆነለት የተሸናፊነትና የዝቅተኛነት መንፈስ አድሮባቸወ ሁሉን አራጊና ፈጣሪ እነዚሁ ቡድኖች

ናቸው በሚል በኢትዮጵያዊነት የታገለውን ሁሉ ሚናውን ይሰርዛሉ። ይህ አሳዛኝ ክስተት ነው። በተማሪው እንቅስቃሴ የታገሉት የትግራይ ሆነ የኤርትራ ተወላጆች የታገሉት በኢት ዮጵያዊነታቸው ነው። ይህ ቀርቶ ወደ ሻዕቢያና ጀብሀ የሄዱትም ከውስጠለ ለውጥ እናመጣ ለን ብለው ሞክረው እንደነበር ሌላጊዜውን ጠብቆ መነገር ያለበት ታሪክ ነው። በዚያን ጊዜ እገሌ ከየት ተወለደ ብሄረሰቡ ምንድነው ብሎ ተጨንቆ የሚጠይቅም አልነበረ። ሁላችንም ኢትዮጵያዊ ነበርን። በመሆኑምበዘመነ ደርግ ዛሬ ዋለልኝን በሲይኤነት ሆነ በሻዕቢያ አገልጋ ይነት የሚከሱት ዛሬ ክስ ደርዳሪዎቹ ኤርትራውያንና የትግራይ ተወላጆች ከሌሎች ጋር ሆነው ጠባቦቹን እየተዋጉ ሲወድቁ የት እንደነበሩ ብንጠይቅ አግባብ አለው።

በአዬው ዘመን የአገዛዛቸው ዋና ደጋፊ አሜሪካና ምዕራባውያን ነበሩ። በኢትዮጵያም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ነመብትና ነፃነት የሚታገሉ ኃይሎች የሚደገፉት በሶሻሊስቱ ጎረ ነበር። ስር ነቀል ለውጥ የሚፈልግ ሁሉ ለአፈሪካ ነፃነትና መብት የሚመኝሁሉ ፀረ ኢምፔሪያሊስት መሆኑ የማይታለፍ ነበር። ዋናው ኢምፔሪያሊስት፣ ዋናው የቀጥታና የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ አባወራና ደጋፊ አሜሪካና ምዕራቡ ነበር። የደቡብ አፍሪካን የአፓርቴይድ ዘረኛ ስርዓት ዋና ደጋፊ አሜሪካ ነበር። የኩባ አብዮት፣ የቪየትናም ትግል፣ የአፍሪካ ፀረ ቅኝ አገዛዝ ትግል፣ የቻይና አብዮት፣ የአውሮጳ የ 1968 ንቅናቄ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ይካሄዱ የነበሩ ሽምቅ ውጊያዎች ወዘተ ሲጤኑ በዚያን ጊዜ ግራ አለመሆን ነበር እንዲያውም በሬሳነ ት የሚያስፈርጀው። ከዚያ አልፎ ተርፎ ደግሞ የሕዝብን እኩከልነት፣ ሕዝባዊ ዴሞክራሲ፣ የሰርቶ አደሩን መብት ፣የሀገር ሉዓላዊነተን የሚፈልግ ሁሉ የምዕራቡ ርዕዮት ተከታይ ሊሆን አይጠበቅም። እኩልነት፣ ዴሞክራሲ፣መብት ወዘተ ካልን ሶሻሊዝም መባሉ አይቀሬ ነበር። ዛሬም ነው። የአሜሪካ ቀኞች ባራክ ኦባማን ሶሻሊስት ብለው እየከሰሱ ያስቁን የለ ? ወጣም ወረደም ግን ያ ትውልድ ለችግሩ መፍትሄ ሊሰጥ የተነሳው በነበረው ርዕዮት አማካኝነ ት ነበር። ይህም ደግሞ የራስን ዕድል የመወሰን መብትን እስከ መገንጠል እስከሚለው ድረስ ያካተተ መሆኑ ለርዕዮቱ እንግዳ ለሆኑት ያደናግር እንደሆነ እንጂ የአቅዋሙ መሰረት ሙሉ መብትን በማወቅ የውዴታ አንድነትን ማስቀደም የሚል ነበር። የመገንጠልን መብት ማወቅ ማለት መገንጠልን መደገፍ ማለት አይደለም የሚለውን የተቀበሉት ተራማጆች የትምክህትን አደጋ ሲረዱ የጠባብነትን መርዝ በሚገባ አላዩትም ተብለው ሊወቀሱ ይችላል። ይህን መሰል ወቀሳ በራሱ ላይ ኢሕአፓ ከዓመታት በፊት አድርጓል። በቀጣይ ፕሮግራሞቹም አርሞ ተገኝቷል። ለማንኛውም ዋለልኝም ሆነ ተራማጆቹ በመላ ሀገር ትገነጣጠል የሚል አቅዋም አልነበራቸውም። መብትን በማወቅ እምነትን ፈጥረን የጋራ ትግልን እናጠናክራለን የሚል እምነት ነበራቸው። ይሄን አቅዋም ስህተት ነው ብሎ መከራከር ይቻላል ነገር ግን የትምክህት አባዋራ ሆነው፣ የሞረሽ ወዘተ አዘጋጅ ሆነው

በጭቁን ሕዝብ ላይ የሚጨፍሩ የነበሩት፣ ዛሬም ኦሮሞን ሕዝቡ በሚፈልገው ስም መጥራት የሚያማቸው፣ አሊያም ተስፈንጥረው ትግሬውን ሁሉ ካልጨረስን የሚሉ አስመሳዮችና የወያኔ የስውር አርበኞች በዚያ ትውልድ ላይ፣ በዋለልኝ ላይ የማይቆረጠም ወሬ ቢቆሉና ቢያሹ ልንቀባላቸው ሆነ ልንሰማቸው አይገባም። በዚያ በታገለ ትውልድ ላይ፣ የወኔ ቋት በሆነው ትውልድ ላይ የጨቋኝ አገዛዞችን ኃጢያትና ወንጀል መላከክ/ማላከክ አይቻልም። ሁሉም የየራሱን መስቀል ይሸከም ተብሏል! ዋለልኝ ሲወገዝና ያልነበረውን ሆነ ሲባል ወይም ለሚወዳት ሀገር ሕይወቱን ሰጥቶ በወጣትነት ተቀጭቶ እየታየ ከመጣው አገዛዝ ጋር እያደሩ ና ኢታሪካዊ ትንተናን እየደረደሩ ሙት ወቃሽ የሆኑትን በዝምታ ማለፍ አይቻልም። ትውልዴን፣ ጓዶቼን ፣ ወንድም እህቶቼን የጨረሱ አገዛዞችን ያገለገሉ ወይም የደገፉ ሲፈነ ጩ ዝምታማ ቢፈጠርብን ኖሮ ድሮም ባላመፅን ባልታገልን ነበር። ዋለልኝ ለኢትዮጵያ ለችግሮች መፍትሄ በመሰለው አቅርቦ በወሬ ብቻ ሳይወሰን በተግባርም ሲታገል ተሰውቷል። ዛሬ ወቃሾች ለመሆኑ ታግለዋል? ለጭቆና መልስ ሰጥተው ነበረ ? ምን መፍትሄ አቀረቡ? መጀመሪያ ይህን ቢመልሱ የሚሻል ነው። በዚያ በታገለ ትውልድ ላይና በእጅ አዙርም በኢሕአፓ ላይ የሚጧጠፈው ዘመቻ አርአያ-ጀግና የነበረውን የሆነውን ዋለልኝን ሲያብጠለ ጥል እነሆ የበኩሌን ወግዱ አቅርቢያለሁ።

- ያ ትውልድ  ጭቆናን በአጠቃላይና የብሄረሰብ ጭቆናን ተቃውሞ በመታገሉ ይኮራ ል፤እኔም እኮራለሁ።
- ያ ትውልድ በሀይማኖቶች መሀል ልዩነት ይቁም ብሎ በመታገሉ ይመሰገናል።
- ያ ትውልድ የአዬውን የጨለማ አገዛዝ ለመጣል ያካሄደው ትግል ሁሉ ክቡር ነው።
- ያ ትውልድ አረመኔውን ደርግ መታገሉ  የሚያስመሰግነው ነው።
- ያ ትውልድ ብሄረሰብ ጎጥ ሳይል ተባብሮ መታገሉ የሚያኮራን ነው።
- ያ ትውልድ ዘር፤ጎጥ ብሄረሰብ  እየመረመረ አልተለያየም፤
- ያ ትወልድ ጠባቦች ገና ብቅ ሲሉ ጀምሮ አጋልጦ የታገለ ሀገር ወዳድ ትውልድ ነው፡
- ያ ትውልድ ለዴሞክራሲ፣ መሬት አራሹ፤ለሰርቶ አደሩ ሕዝብ መብት ወዘተ የታገለና ታሪካዊ አስተዋፅዖ ያደረገ ነው።

" የታገለው ሞቶ የታገለው ጠፍቶ
ያልታገለው ኖሮ ያልታገለው በዝቶ
ያ የታገለውን ያልታገለው ወቅሶ
የምጣዱ ሳለ የዕንቅቡ ተንጣጥቶ
ጉድ ታሪክ ተብሎ ቅጥፈት ሀቅን ገድሎ
ሀገር ሁሉ ክርፋት ግም ሽቶ ተብሎ
የመሀይም መንጋ በምሁር ተፈርጆ"።

ዋለልኝ መኮንን የኢትዮጵያ ብርቅዬ ልጅ ነበር። እስቲ የታገለውን መዝለፍና መጨፍጨፉ ቆሞ ፤ምላስን ገደብ አድርገን በትግሉ ተሰልፈን የራሳችንን አኩሪ ታሪክ እንፃፍ! ዋለልኝ የኢሕአፓ ነበር፤ ኢሕአፓም ይኮራበታል። ለሀገራችን ችግር መፍትሂ ፈለገ እንጂ የሚወዳት ንና የሞተላትን ኢትዮጵያ ሊጎዳት አልተነሳም ነበር። በዚያ በነበረው ተጨባጩ ሁኔታ ያ ትውልድ ሀገራችንን ለማዳን ተዋድቋል። ዛሬ ከ 40 ዓመት በኋላ ሌላ መብራት አብርቶ መውቀሱ አይበጅም። አፄ ምኒሊክ መድብለ ፓርቲ ለምን አላቋቋሙም ብሎ መውቀስ ዓይነት ነው። ዋለልኝና መሰሎቹ በኢትዮጵያዊነታቸው የኮሩ፤ደፋርና ቆራጦች፤ ለማንም ፈረንጅ ያልተጎነበሱ ጀግኖች ነበሩ፤አሁንም ናቸው። ለዚህም ነው በዋለልኝና በዚያ ትውልድ ላይ የሰነፍ ምላሰኛ የሆኑት ሁሉ በከንቱ የሚባዝኑት። አዋጅ ለአዋጅን ለፃፈውና የስነ ፅሁፍ ችሎታ ለነበረው ለደብተራው ጓደኛ ለዋለልኝ የበኩሌን ግጥም ብጤ አቅርቤ ልሰናበት፤

" ሌባ ጣት ቀስረው በሀሰት የከሰሱ
ለሀቅ የቆሙትን በውሸት ያጠቁ
ሌሊቱ ሲነጋ ሁሉም ተጋለጡ
በባዕድ መዲናም አልቻሉም ሊጠፉ
የሀሳዊ መሲህ ታሪክ ሁሌም ክፉ።

....

ታሪኩን የረሳ ቅርሱን የዘነጋ
የሞተለትንም ያልሰጠ ምስጋና
ጠላት ይገዛዋል ባሪያ አድርጎ ቀጥቅጦ
ማን ሊያዝንለት ይሆን እሱ ራሱን ጥሎ።።

ራሳቸውን የጣሉ ፀረ ታሪኮች የዋለልኝን ስም አያጎድፉም!!!!